# ዋሺንግተን ዲሲ የእሳት እና ድንገተኛ ሕክምና አገልግሎቶች መምሪያ
## የእሳት መከላከያ ክፍል – ጠቅላይ እዝ

| | |
|---|---|
| **ርእሰ-ጉዳይ: ፓይሮቴክኒክስ** | **ጠቅላይ እዝ:** 609 |
| **ክፍል:** እቆዶች እና ፈቃዶች | **የወጣበት ቀን:** ጥቅምት 1, 2009 |
| **ባለስልጣን:** DCMR 12, ምዕራፍ 12H, ክፍል F-107H<br>የእሳት መከላከል ደንብ ማጠናከሪያ | **አገልግሎት የሚያበቃበት ቀን:** እስከ ሚወገድ ድረስ |

**I. አድማስ**

በዚህ ሰነድ ውስጥ የሚገኘው መረጃ ለሁሉም ከዲሲ እሳት እና ድንገተኛ ሕክምና አገልግሎቶች መምሪያ የእሳት መከላከል ክፍል የፓይሮቴክኒክስ ፈቃድ ለማግኘት የሚጠይቁ አመልካቾች ያገለግላል።

**II. አላማ**

የዚህ ጠቅላይ እዝ የፓይሮቴክኒክስ የመጠቀም እና የመለቀቅ ቦታ እና የፍጻሜዎች ማከናወኛ ፈቃድ ጥያቄዎች አቀባበል እና ክንውን ሂደት ደረጃው የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ነው።

**III. የቃላት ፍቾ**

የለም

**IV. ፖሊሲ**

በአንድ በኩል የፓይሮቴክኒክስ መጠቀሚያ ቦታዎች እና ፍጻሜዎች ማከናወኛ ፈቃዶች ጥያቄዎች ጉዳይ ብቁ እና ስርአት ባለው አካሄድ እንዲሁም ያለምንም መዘግየት ማከናወን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የማህበረሰቡን፣ የአከናዋኞችን፣ እና የተቆጣጣሪዎችን ደህንነት ማረጋገጥ እንዲሁም ህጎች፣ ደንቦችን እና ስነስርአቶች አክብሮ መስራት የእሳት ማርሻል ጽሕፈት-ቤት ፖሊሲ ነው።

**V. አሰራር**

ፓይሮቴክኒክስን (1.4ግ) አንዳንድ ጊዜ በስህተት ርችት ተብሎ ይጠራል። የስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች እና የህዝብ ስብሰባዎች ላይ ህብር ለመፍጠር ጥቅም ላይ ይውላሉ። ወደ ሚተኮሱበት ቦታ በሜትሮፖሊታን ፖሊስ መምሪያ <u>ሳይታጀቡ</u> መጓጓዝ ይችላሉ።

**ሀ. <u>እቤት ውስጥ እና ከቤት ውጪ ማሳየት</u> (IFC ምዕራፍ 33, NFPA 1126)**

1. ሁሉም የተሞሉ የፈቃድ ማመልከቻዎች እና ለዲሲ ግምጃቤት ተከፋይ የሚሆኑ ትክክለኛ መጠን የያዙ የቼክ ወይንም የገንዘብ ትእዛዞች ወደ የእሳት ማርሻል ጽሕፈት-ቤት በአካል በመሄድ ማስረከብ የግድ ይላል። (ማስታወሻ: ማመልከቻው በእሳት ማርሻል ጽሕፈት-ቤት እና ኦንላይን ላይ ይገኛል)።

**ሁሉም እቅዶች ፍጻሜው ከሚጀመርበት ጊዜ ቢያንስ ከ 10 የስራ ቀናቶች በፊት ማስረከብ ያስፈልጋል።**

2. የተኩሱ እቅድ ከማመልከቻው ጋር ማስረከብ ያስፈልጋል። እቅዱ የሚከተሉትን ያሟላ መሆን አለበት:

ሀ. ምርቱን ስፖንሰር ያደረገው ሰው፣ ቡድን፣ ወይም ድርጅት ስም።
ለ. ምርቱ ጥቅም ላይ የሚውልበት ቀን እና ሰአት።
ሐ. ትክክለኛ የምርቱ ቦታ።
መ. ፓይሮቴክኒኮቹን የሚተኩሳቸው ሰው ስም (በሌላ አባባል፣ የፓይሮቴክኒኩ ባለሙያ)።
ሠ. የሁልም በቦታው የሚገኙ ረዳቶች ብዛት ቁጥር፣ ስሞች፣ እና ዕድሜ።
ረ. የፓይሮቴክኒኩ ባለሙያ የብቃት ማረጋገጫዎች።
የባለሙያው የፓይሮቴክኒክ የስራ ልምድ።
ሰ. ባለሙያው ወይንም ረዳቱ(ረዳቶቹ) የግዛት ወይንም የፌዴራል ፈቃድ እንዳላቸው ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው።
ሸ. የመድህን ድርጅቱ ወይንም የገንዘባዊ ሀላፊነት ያለው አካል ማረጋገጫ።

ማስታወሻ: ሁሉም የመድህን ሰነዶች ወደ የዲሲ እሳት እና ድንገተኛ ሕክምና አገልግሎቶች ጠቅላይ ነገረፈጅ ተልከው ተቀባይነት እንዳላቸው መረጋገጥ አለበት። ከዲሲ እሳት እና ድንገተኛ ሕክምና አገልግሎቶች ጠቅላይ ነገረፈጅ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እስከሚሰጥ ድረስ ፈቃዶች አይሰጡም። ይህ የ 10 ቀኑ የማመልከቻ መስፈርት አላማ ይህ ነው።

ቀ. ጥቅም ላይ የሚውሉት ፓይሮቴክኒክ መሳሪያዎች ብዛት እና አይነት፣ ባለሙያው ከመሳሪያዎቹ ጋር ያለው የስራ ልምድ፣ እንዲሁም የረዳቶቹ አጠቃላይ ሀላፊነቶች መግለጫ።
በ. ምርቱ የሚቀመጥበትን ቦታ የሚያሳይ ስእላዊ መግለጫ። ይህ ዳያግራም የፓይሮቴክኒክ መሳሪያዎቹ የሚተኮሱበት ልዩ ቦታ፣ በትርኢቱ ጥቅም ላይ የዋሉ ፓይሮቴክኒኮች የሚወድቁበት ቦታ ስፋት፣ እና ተመልካቹ የሚወሰንባቸው መስመሮችን ማሳየት አለበት።
ተ. የፓይሮቴክኒክ መሳሪያዎች የሚገጣጠሙበት ልዩ ቦታ።
ቸ. የፓይሮቴክኒክ ማቴርያሎች እና መሳሪያዎች ባህሪ እና ማከማቻ ቦታ።
ኀ. ጥቅም ላይ የሚውሉት የፓይሮቴክኒክ ማቴርያል(ሎች) ደህንነት መረጃ ወረቀት።
ነ. የሚተኮሰው መሳሪያ ማስቀመጫ፣ እይታ፣ እና መገጣጠሚያዎቹ በተፈጥሮአቸው እሳትነታቸውን መቀነስ በሚያስች አኳኋን የተሰሩ መሆናቸው የሚያሳይ ማረጋገጫ።
ኘ. በመውደቂያ ቦታው ላይ ትርኢት የሚያሳዩ ሁሉም ባለሙያዎች የሚለብሷቸው ማቴርያሎች በተፈጥሯቸው እሳት መከላከል ወይንም ማቀዝቀዝ የሚችሉ መሆናቸው የሚያሳይ ማረጋገጫ።

3. ለዲሲ ግምጃቤት ተከፋይ የሚሆኑ ትክክለኛ መጠን የያዙ የቼክ ወይንም የገንዘብ ትእዛዞች።

4. ፈቃዶች የሚሰጡት አጥጋቢ የቦታ ፍተሻ ከተደረገ በኋላ ነው።

ማስታወሻ: ሁሉም ከፓይሮቴክኒክ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች ወደሚከተለው አካል መላክ አለባቸው:


**District of Columbia**
**Fire & Emergency Medical Services Department**
**Fire Prevention Division**
**1100 4th Street SW Suite E700**
**Washington, DC 20024**
**(202) 727-1614**